# ለዴሞክራሲ አርበኞች - ተባብሮ ለመታገል የሚያስችል ቀላልና ጠቃሚ ሃሳብ

በጣሰው tassat@t-online.de

## ለጊዜው በእጅ የገባችሁ በውጭ የምትገኙ 19 የ8 ዘውጋዊ እና 13 ዜጋዊ ድረጅቶች

1. Oromo Lieberation Front (OLF).................................. የኦሮሞ ነጻነት ግንባር
2. Front for Independence of Oromia (FIO) ......................... የኦሮሚያ ነጻነት ግንባር
3. Oromo Iieberation Front "United" (OLFU) .......................የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ሕብረት
4. Oromo Democratic Front (ODF) ..................................... የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር
5. Bete Amara ....................................................................ቤተ አማራ
6. Amhara Democratic Forces Movement..............................የአማራ ዴሞክራሲያዊ ሃይል ንቅናቄ
7. Amara People´s Medhin Movement .................................የአማራ ሕዝብ መድህን ንቅናቄ
8. All Amara Organization II ................................................. ዳግማዊ መአሕድ
9. Amara People´s Movement ...............................................የአማራ ሕዝብ ንቅናቄ
10. Moresh Wogene Amara Organization ................................ሞረሽ ወገኔ የአማራ ድርጅት
11. Gambela People Lieberation Movement............................ የጋመቤላ ሕዝብ ነጻነት ንቅናቄ
12. Ogaden National Lieberation Front ....................................የኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግንባር
13. Benishangul People Lieberation Movement........................የቤኒሻንጉል ሕዝብ ነጻነት ግንባር
14. Sidama National Liberation Front (SNLF) ........................የሲዳማ ብሔራው ነጻነት ግንባር
15. Sidama National Democratic Movement ...........................የሲዳማ ብሔራው ዴ. ንቅናቄ
16. Afar People´s party (APP) ..................................................የአፋር ሕዝብ ፓርቲ
17. Afar Revolutionary Demokratic Unity Front ....................የአፋር አብዮታዊ፤ ዴ. ግንባር
18. Tigray People´s Democratic Movement ............................የትግራይ ሕዝብ ዴ. ንቅናቄ
19. TAND (Tgrians for democrciawi Tibibir)..........................ትግራወያን ለዴሞክራሲያዊ ትብብር

1. Patriot G7.................................................................................አርበኞች ግንቦት7
2. EPRP ..........................................................................................ኢሕአፓ
3. EPRP UNITED ..............................................................................ኢሕአፓ አንድነት
4. MEI´SONE .......................................................................................መኢሶን
5. MEDHIN ........................................................................................መድህን
6. Bruh Ethiopia ........................................................ ብሩህ ኢትዮጵያ
7. Ethiopian National Transitional Councel ..................................(የሽግግር ምክር ቤት)
8. Ethiopian Youth Movement ........................................................የኢትዮጵያ ወጣቶች ንቅናቄ
9. Ethiopian Democratic Unity .......................................................(ሕብረ ሕዝብ)
10. Patriotic Movement II .............................................................ዳግማዊ ያርበኞች ንቅናቄ
11. Susa Ethiopian Renocance Democratic Organization ................ሱሳ የኢ. ት. ዴ. ድ
12. Commen Movement for the New Ethiopia .................................ለአዲስቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ
13. Ethiopian Youth Tegadlo Movement .........................................የኢትዮጵያ ወጣቶች ተጋድሎ ንቅናቄ

**አስቀድሞ የከበረ ሰላምታ ይድረሳችሁ፤**

**በዚህ ማስታወሻ የቀረበውን ሃሳብ ጠቃሚ ነው የምትሉ ስለጠቀሚነቱ፤ ጎጂ ነው የምትሉም ስለጎጅነቱ የሚታያችሁን ምክንያቶች ጨምራችሁ መልስ እንድትሰጡ ትጠየቃላችሁ፤ ሌሎች ይህ ሃሳብ ከተላለፈበት ዕለት ቀደም ብሎ ተደራጅታችሁ እንቅስቃሴ የጀመራችሁና በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያልገባችሁ ካላችሁ ተቀላቅላችሁ ድምጻችሁን ማሰማት ትችላላችሁ። በጉዳዩ ላይ ድምጽ ለማሰማት ግለሰቦችም መብታችሁ የተጠበቀ ነው። መልስ ስትሰጡ ግን አድራሻችሁን ማኖር አትርሱ። የመልሱ ውጤት ከታየ በኋላ ቀጣይ ሂደት ይኖራ ተብሎ ተስፋ ይደረጋል።**

**ለዚህ ጽሁፍ መነሻ፤-** ከወራት በፊት አቶ ዘውዴ ጉደታ የተባሉ ወንድም *"የኢትዮጵያ አገራዊ ንቅናቄ እና የአገር አንድነትን "ያገቱት" ሦስት ተጻራሪ ሃይሎች"* በሚል ርዕስ አንድ ሰፋ ያለ ጽሁፍ አስነብበው ነበር። ከዚያም በላይ የጸሃፍያን ድምጾች በሚል የኢሳት አምድ ላይ ቀርበው ከጋዜጠኛ ርእዮት አለሙ ጋር እሰጥ አገባ ብለውበታል። እንደተከታተላችሁት ተስፋ ይደረጋል፤ ካላያችሁትም የ www.borkena.com ን ደጅ ምቱ፤ ይከፈትላችሁማል። የአ ሁኑ  አነሳስ ግን ስለጽሁፉ ለማውራት አይደለም። በዚህ ጽሁፋቸው 3 አጋቾች ብለው የፈረጇቸው ሶስት ተጻራሪ ሃይሎች ተዋንያን የሚከተሉት

*1. የኢትዮጵያ አንድነት ሃይሎች፤*

*2. የመገንጠልን አጀንዳ  የሚያራምዱ ወገኖች፥*

*3. የህወሐት የገዢ ቡድን"* ሲሆኑ፤ ማስታወሻው የሚያጠነጥነው በነዚህ 3 ሃይሎች ዙሪያ ቢሆንም፤ በተለይ የሚያተኩርበትና ክብደት የሚሰጠው ግን፤  ቡድን 1 እና 2  ላይ ይሆናል።

በእርግጥም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ችግር በውስጥ በኩል ሰብሰብ ተደርጎ ሲታይ፤ የሚዋልለው በአነዚህ ሶስት ሃይሎች መካከል መሆኑን መገንዘብ የሚያስቸግር ባይሆንም፤ በሕዝብም መካከል ያለው ሁኔታ ሲታይም ብዙ ልዩነት አይኖረውም። በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቡድኖች ላይ በመቆየት፤  ሃይላቱ እናንተ የምትሟሟቱለት  የየራሳቸሁ የሆነ ጥያቄ ያላችሁ መሆኑና ይህንን ጥያቄያችሁን ምን ብታረጉ ነው መልስ አስገኝታችሁለት እናንተም፤ ሃገሪቷም፤ እፎይ ብላችሁ፤ እንቅለፍ የሚወስዳችሁ? ከሚል አቅጣጫ ለማየት ይሞከራል። ጥያቄዎቹ ዘመን የተሻገሩና መፍትሄ  ተገኘላቸው ሲባል መልሰው ጥሬ ሲሆኑ፤ ጠበቡ ሲባል ሲሰፉ፤ አጠሩ ሲባል ሲረዝሙ፤ ተሟሟቁ ሲባል ሲቀዘቅዙ፤ አንዴ ሲወጡ፤ ሌላ ጊዜ ሲወርዱ፤ የቆዩ እንጂ ለዛሬ አዲስ ሆነው የሚቀርቡ አይደሉም። አዲስ ይሆናል ተብሎ የሚታሰበው በጥያቀዎቹ በኩል ሳይሆን፤ በመፍቻቸው በኩል ነው። ተከታተሉ፤

"የኢትዮጵያ አንድነት ሃይሎች" ቡድን፤  የመንግስተሰማያት መግቢያው አስፋልት መንገድ አንድነት የሚባለው አውራ ጎዳና ብቻ ነው ሲል፤ "የመገንጠልን አጀንዳ  የሚያራምዱ ወገኖች" ደግሞ፤ ሰው ሳይገለጥለት ቀርቶ ነው እንጂ፤ ወደ መንግሥተሰማያት ቀጥ አድርጎ የሚወስደው  መንገድ ጊዜ አጥቼ ተጉዤበት ባላየውም፤ መገንጠል የሚባለው አውራ ጎዳና ይመረጣል ቢል፤ እናንተ ሁለት ወገኖች በተለያየ ጎራ ሆናችሁ ያነሳችኋቸው ጥያቄዎች እያንዳንዳችሁ ያለችሁ የዴሞክራያዊ መብት መዕቀፍ የሚፈቅድላችሁን ከማድረግ ያለፈ አለመሆኑን፤  ማንም  ጨዋ አገር ወዳድ ዴሞክራት ቢሆን፤ ጥያቄ ውሰጥ አያስገባውም። ይህም ማለት እነዚህ ጥያቄዎች የኮሩ፤ የደሩ፤ ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች ናቸው ማለት ነው። ዕውነቱ ይህ  ሆኖ እያለ ታዲያ፤ እናንተ ሁለት ወገኖች እነዚህ መብቶቻችሁ ችግር ቀፍቃፊ ሆነውባችሁ፤  እርስ በርስ ወደመባላት የደረሳችሁበት ምክንያት ምንድነው? ብለን ብንጠይቅ፤ መልሱ ችግር ቀፍቃፊዎች የመብት ጥያቄዎቹ ሳይሆኑ፤ ችግር ቀፍቃፊዎቹ፤ የጥያቄዎቹ መልስ ሰጭዎች፤ መልስ ይሰጣሉ ብላችሁ የምትከተሏቸው የመልስ አሰጣጥ ዘዴዎች ናቸው። ለዴሞክራሲያዊ ጥያቄ መሰጠት የሚገባው መልስ ዴሞክራሲያዊ መሆን ሲገባው፤ ጸረ-ዴሞክራቲክ ዘዴ በመጠቀም፤ ጉዳዩ "ፍየል ወደዚያ ቅዝምዝም ወደዚህ" እንዲሉ፤ ጥያቄው ወዲህ መልስ ወደዚያ እየሆነ ነው። ወይም እነዚህን ዴሞክራሲያዊ መፍትሄዎች ለማስገኘት የሚያስችል አመች ሜዳ አለመኖር ነው። ያም ሆነ ይህ ታዲያ ለዴሞክራሲያዊው ጥያቄ  ዴሞክረሲያዊ መልስ ለመስጠት፤  ዘዴው  ምንድነው? ወደሱ ይታለፋል፤ ከዘዴው በፊት ግን፤ ዘዴውን ስራ ላይ የሚያውሉ የግድ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ያስፈልጋሉና እነዚህ ዴሞከራቶች ደግሞ ዴሞክራት መሆን ብቻ ሳይሆን፤ አርበኝነትንም ስለሚጠይቃቸው፤ "የዴሞክራሲ አርበኞች"ን ተዋወቁ፤

**ስለዴሞክራሲ አርበኞች፤-**

*አረረም መረረም፤ ሞቀም ቀዘቀዘም፤ ምንም ሆነ ምንም፤ ነጻ የሕዝበ ውሳኔን አክብረው  የሚቀበሉ፤ ለመቀበል ዝግጁ የሆኑ፤ ነጻው የሕዝብ ውሳኔ እንዲሳካ የበኩላቸውን ያልተቆጠበ ጥረት የሚያደርጉ፤ ውሳኔውን ከማንኛውም አደጋ ለመጠበቅ ቁርጠኝነትን የሚያሳዩ፤  ዴሞክራሲ ሁልጊዜም የምህረት አምላክነቱ የሚረጋገጠው የሚያጣም የሚያገኝም በሱ ፊት እኩል መሆኑን የሚያስተምሩ፤ ዴሞክራሲው ያስገኘለትን እንጂ፤ እሱ የፈለገውን ማግኘት አለመቻልም ስላለ ያንን ክስተት ችሎ በጽናት ማለፍን ስለሚጠይቅ፤ ለዚህ ጠንካራ ሆኖ ለመገኘት የሚተጉ ሁሉ፤  የዴሞክራሲ አርበኞች ናቸው። ለምንድነው የዴሞክራሲ አርበኞች የሚባሉት፤ የሚል ጥያቄ ካለ፤ ጉዳዩ እንዲህ ነው። ምንም እንኳን ባሁኑ ጊዜ ለዴሞክራሲ፤ የዴሞክራሲ ትግል፤  ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፤ የሚባሉትን ቃሎችና*

ሃረጎች ማራገብ ለኢትዮጵያውያን የጥርስ መፋቂያዎች ናቸው ቢባል፣ ስህተት ባይሆንም፣ እያንዳንዱ አራጋቢ ድርጅትም ሆነ ግለሰብ እራሱ ምን ያህል ዴሞክራት እንደሆነ የመረጋገጡ ጉዳይ ግን አስቸጋሪ ነው። አስቸጋሪ የሚሆንበትም ምክንያት፣ ድርጅቶችም ሆኑ፣ ግለሰቦች ዴሞክራሲውን ሲፈሩት ይታያል። ጥያቄ ጥያቄን ስለሚወልድ፣ አሁን ደግሞ፣ ለምንድነው የሚፈሩት? የሚለው አይቀሬ ይሆናል፣ ለመልሱ የሚከተለውን ማየት ቢሞከር፣

በኢትዮጵያችን የአንደነት ሃይል ነኝ የሚለው ወገን፣

- በዴሞክራሲም የሃገር መገነጣጠል ሊመጣ ይችላል በማለት፣

- ከዚሁ ዙረያ ሳይወጣ፣ ፈንጠር ብሎ ደግሞ፣ አንድ ቀን የኔ ፓርቲ በዚች አገር ላይ ስልጣን ይዞ እከሌ የተባለው ፓርቲ አስተዳደር - የዴሞክራቶቹ ፓረቲ ወይም የሪፓብሊካኖቹ ፓረቲ፣ የክርስቲያን ዴሞክራቱ ወይም የሶሻል ዴሞክራቱ ፓረቲ አስተዳደር እንደሚባለው - ሲባል የመስማቱ ምኞት፣ በዴሞክራሲ ስለመሟላቱ እርግጠኛ ባለመሆን፣

- ከአንድነቱ ጎራ በተቃራኒ የቆመው ደግሞ፣ ተገንጥሎ እራሱ የሚያስተዳድራት ግዛት ኖሮት፣ ሌላው ቢሳካ ባይሳከም፣ ቢያንስ ግን ባንዲራው በተባበሩት መንግስታት ግቢ ስትውለብለብ የማየት ሕልም ያለው፣

- አንዱ ወይም ሌላው፣ አሁን ባለው ሥርዓት ያገኘሁት ጥቅም አለ፣ እሱስ ይቀጥል ይሆን?

- ስለነገዋ ኢትዮጵያም ዛሬ ሳይሆን፣ ነገ ወያኔ ከወደቀ በኋላ ብንነጋግር የሚልም ዘይቤ ያለው፣

- የመሳሰሉ ጉጉቶችና ምኞቶች በዴሞክራሲ ሊገጥማቸው የሚችለውን ዕድል መገመት ባለመቻል፣ ፍሃት ስለሚኖራቸውና በምክንያቱም ለዴሞክራሲ ሊኖራቸው የሚገባውን ተዓማኒነት የሳሳ ስለሚያደርገው፣ - ፈሩ ሲባልም ታዲያ፣ ፍርሃትን ዋጋቢስ ለማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ እንደሁኔታውና እንደሚባለውም፣ የፈራ የናቱ ልጅ ነው፣ ፍርሃት የጥበብ መጀመሪያ ነው የሚሉ ገጽታዎች እንዳሉትም በመዘንጋት መሆን አይኖርበትም፣ በምንም መመዘኛ ግን በዚህ ምክንያት ወደ ጠብ አይኬድም። - ፍራሃቶቹን አልፎ የዴሞክራሲን አሸናፊነት በሙሉ ልብ ተቀብሎ፣ ማጣቱም ሆነ ማግኘቱ፣ ሁለቱም ፍትሃዊ ናቸው በማለት ለፍትህ ተገዥ መሆንን ማረጋገጥ የሚያስችለውን ጽናት መላበስን ይጠይቃል ለማለት ነው። ለዚህ የታደሉት ናቸው የዴመክራሲ አርበኞች የሚባሉት። ማስተዋወቂን አጠር ለማድረግ፣ የማይረሳ ምሳሌ ቢነሳ፣ የመለስ ዜናዊ የ1997 "እንከን የለሽ ምርጫ" ሲታወስ፣ መሌ ማግኘትን ብቻ ስለነበረ የሚጠብቀው፣ ማጣት ሲመጣ ትንፋሽ አጠረውና እንከን በእንከን አድረጎ አጨመላለቀው። ልክ ነው? ማብራሪያው በዚህ ላይ ይበቃል። ወደ ዘዴው በመመለስ፣

ዘዴ፣- የኢትዮጵያ አንድነት ሃይሎች እና የመገንጠልን አጀንዳ የምታራምዱ ወገኖች፣ በቅድሚያ ማድረግ ብትችሉ፣ አንዱ የሌላውን ጥያቄ ማክበር፣ የያዝከውን አላማ እርግፍ አድርገህ ትተህ፣ እሱን የነካህበትን እጅ በበረኪና ታጥበህ፣ ክርስትና ተነስተህ፣ ወይም ማተብህን በጥሰህ ወዘተ… የሚል ቅድመ ሁኔታ መደርደር አስፈላጊ እንዳልሆነ መገንዘብ፣ እነዚህን ጥያቄዎች/ቅድመ-ሁኔታዎች ማቅረብ ማለት፣ አንተን አሁን ባለህበት ሁኔታ ሳይሆን፣ ሌላ ገጽታ ይዘህ ና እንደማለት ስለሚቆጠር፣ ባጭሩ አንተን አላውቅህም እንደማለት ነው የሚሆነው። አንድም አላማን ሆነ፣ የትግል ዘዴን የሚያስቀይር፣ ማንኛውንም ጉደይ ተውልኝ፣ ጨምርልኝ ወይም ለነገ ያዝልኝ፣ የሚባል ነገር ማንሳት ሳይኖር፣ ሁለታችሁም ወገኖች ከዛሬ ስንት ዓመት፣ ከዛሬ ስንት ወር ጀምራችሁ አንግባችሁ ያቆያችኋቸውን የየግል ጥያቄዎች ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ወደኋላ በማቆየት፣ የትግል ጉዞዋችሁን ከዚህ በታች በክፍል አንድና ሁለት በተቀመጡት አቅጣጫዎች ብታደርጉና በመጨረሻም ወደ ክፍል 3 ተሸጋግራችሁ፣ ሩጫችሁን ብትጨርሱ፣

**ክፍል 1**

***መተማመኛችሁ***

*ሀ. ኢትዮጵያ ተብላ የምትጠራ፣ ዓለም ያወቃት፣ ጸሃይ የሞቃት፣*

*ለ. ሶስቱን አጋቾችና ሌሎቻችንንም ጨምሮ ዜጎቿ የሆንን፣*

*ሐ. ኑሮ "እንደሚባለው" ለአንደኛው ወገን ለስላሳ፣ ለሌላው ሻካራ ሆና የኖረችና ያለች፣*

*መ. ዛሬ በትግሬ ሕዝብ ነጻነት ግንባር የተዘረጋ ዘረኛ የባርነት አገዛዝ ስር የምትገኝ አገር አለችን። !!*

**የትግል ዓላማ ፤- "የህወሐት የገዢ ቡድን " የዘረጋውን የባርነት አገዛዝ አስወግዶ ነጻነትን እጅ ለማድረግ፤ የተባበረ የነጻነት ትግል ማካሄድና፤**
**በወደቀው ስርዓት መቃብር ላይ ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያን ዕውን ማድረግ፤**

**ክፍል** 2
**የዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያ ዕውን የመሆን ሂደት፤**

**የሽግግር መንግሰት፤**
**በተወገደው ስርዓት ምትክ፤ ሥርዓቱን በማስወገድ የታገሉትና ሌሎች ያገባናል የሚሉ፤ ድጋፍ ሊሆኑ የሚችሉ ሃይሎች ሁሉ፤ የተሳተፉበት የሽግግር መንግሥት ማቋቋም፤**

**የሽግግር መንግሥት ተግባራት**
*ሀ.* **የተመረጠ ቋሚ መንግሥት ተፈጥሮ፤ የሽግግሩ ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ ሃገርን ማስተዳደር፤**

**ለ. ነጻና ፍትሃዊ በሆነ ምርጫ የሚመጣውን ቋሚ መንግሥት ለማወጅ የሚያስችሉትን ግብዓቶች እንዲሟሉ ማድረግ፤ - በዚህ**
**ውስጥ የሚካተቱትን ሁሉንም አሁን መዘርዘር ለጊዜው አስፈላጊ ባይሆንም፤ አንዱንና ዋና የነገሮች ሁሉ መቋጠሪያ የሚሆነውን**
**"የመተዳደሪያ ደንብን" (ሕግ-መንግሥን ማዘጋጀት) ሲሆን፤ ለዚህ ሕገ-መንግሥት ግብዓት ይሁኑ በሚል ቀርበው፤ ሕዝብ**
**ይሄኛው ይያዝ፤ ያኛው ይጣል፤ በሚል ብይን የሚሰጥባቸው ነጥቦች ደግሞ፤**

1**ኛ/ እናንት ሁለት ቡድኖች ዛሬ አንስታችሁ በቀጠሮ ያቆያችኋቸውና ሌሎች የምትጨመሩት ካላችሁ፤**

2**ኛ/ ለአቅመ ሄዋንና ለአቅመ አዳም የደረሱ እትዮጵያውያን ሁሉ፤ ቢሻቸው በቡድን ያለያም በግለሰብ የሚያቀርቧቸው፤ በሰማይ የሚበሩ፤**
**ባህር ላይ የሚንሳፈፉ፤ በመሬት ላይ የሚርመሰመሱ ሁሉ፤ አንዳችም እቀባ ሳይደረግባቸው የሚቀርቡ ነጥቦች ቢሆኑ።**

***ለመቋጠሪያ፤*** **ከአቶ ዘውዴ ጽሁፍ** ***"...ሁሉም ጥያቄዎች የማያዳግሙና የዚያች አገር ጉዳይ በሚያገባቸዉ ወገኖች ሁሉ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸዉ መልሶች ሊሰጧቸዉ ይገባል፡፡ ሁሉንም የሕዝብ ጥያቄዎች በአጥጋቢ ሁኔታ መመለስ የሚያስችል መንገድ መከተል ..."*** **የሚለው እዚህ ላይ ተዳብሷል። በዚህም ወደ**
**ከፍለ** 3

**ክፍል** 3
***መደምደሚያ፤***
**"ወያኔ እኮ የራሱን ሕገ-መንግስት አላከብር ብሎን" እየተባለ የሚቆዘምበት፤ ተቃዋሚ ፓረቲ፤ ጋዜጠኛ፤ የጋዜጣ አዟሪ፤ የእድር ማሕበር፤ ቤተክርስቲያን፤ መሰጊድ፤ የሰንበቴ ማህበር፤ የማርያም፤ የሚካኤል ጽዋ ማህበር፤ የወፎች ፉጨት፤ የቅጠል ኮሽታ፤ ሁሉንም መደርደር አይቻልም... ወዘተ. ሳይቀር ከሚንደው የወያኔ ሕገ-መንግሥት ተላቅቆ፤ ሕዝብ እራሱ በጣፈውና እና እራሱ በሚያዝበት፤ መናድ ከፈለገም የሰው ሕገመንግሥት ንደሃል ተብሎ የማይጠየቅበት፤ እሱ እራሱ የሚንደው፤ የጠንካራ ሕገመንግሥት ባለቤት በመሆን፤ የምትፈለገዋን ዴሞክረሲያዊ ኢትዮጵያ ፈጥሮ ቁጭ ቢባል! ምን ይመስላችኋል?**

**ማሳሰቢያ**

1. **እነዚህ ስብስቦች በዚህ ዝርዝር ውስጥ አልተያዙም - ምክንያት ትልልቆችንና ትንንሾቸን ላለማደባለቅ፤**

   1. Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)
   2. Peoples Alliance for Freedom & Democracy (PAFD)

3. United Movement for Salvation of Ethiopia through Democracy
4. Ethiopian National Movement

ኢትዮሚድያ - Ethiomedia.com
April 27, 2017